# የልጅዎ ሐኪም በ ኮቪድ-19 ወቅት ሊረዳዎት ይችላል — ብቻዎን አይደሉም!

## ለ... ወደ ሐኪምዎ ቢሮ ይደውሉ

- ከልጅነት ክትባቶች መርሃግብር አይውጡ። ክትባቶች በአግባቡ የማይወሰዱ ከሆነ ፣ እንደ ኩፍኝ የመሳሰሉ ለመከላከል ለሚቻሉ በሽታዎች ልንጋለጥ እንችላለን።
- በታዳጊ ልጅዎ ወይም በወጣት (ከ13-19 እድሜ) ልጅዎ የባህሪ ወይም የስሜት ለውጦችን በተመለከተ እገዛን ያግኙ።
- ለምግብ ፣ ለመኖሪያ ቤት እና ለሌሎችም ፍላጎቶች ግብአት የሚሆኑ ነገሮችን ለመለየት ይረዳል።
- ስለ መብላት ፣ መተኛት ፣ መሽናት ወይም መፀዳዳትን በተመለከተ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።
- ልጅዎ ቀጠሮ የሚያስፈልገው እንደሆነ አጣርተው ይወቁ።

## ክሊኒኮች ደህንነትዎን ለመጠበቅ ለውጦችን አድርገዋል:

- ጉብኝቶች በስልክ ወይም በቪድዮ እንዲደረጉ
- ለሕፃናት የጤና ምርመራ ጉብኝቶች የተለየ መግቢያ ወይም በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ክፍሎች እንዲኖሩ
- በታካሚዎች ልውውጥ መካከል ጥብቅ የሆነ ጽዳት እንዲደረግ
- በታካሚዎች መጠባበቂያ ክፍሎች ውስጥ ትንሽ ወይም ምንም የጥበቃ ጊዜ እንዳይኖር ማድረግ
- በክሊኒኩ ውስጥ ጥቂት ሰዎች ብቻ እንዲቆዩ መፍቀድ
- "ከአሽከርካሪ ሳይወጣ የሚደረግ አገልግሎት/Drive through" አማራጮችን ማዘጋጀት



ቀጠሮ ለማስያዝ ለልጅዎ ክሊኒክ ይደውሉ። ክሊኒክ ለማግኘት እገዛ የሚፈልጉ ከሆኑ ለእርዳታ ወደ 'Help Me Grow Washington Hotline' ስልክ ቁጥር1-800-322-2588 ላይ ይደውሉ።